**የመንገድፈንድፅ/ቤት**
**ፕሬስመግለጫመስጫቅጽ**
**የኮርፖሬትኮሙዩኒኬሽንዳይሬክቶሬት**

የመንገድ ትራንስፖርት ትልቁን የትራንስፖርት ድርሻ በሚይዝበት አገር የመንገድ መሰረተ ልማት ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ መንግስት የመንገድ ትራንስፖርትን የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ዘርፈ ብዙ እርምጃዎችን ስወዝድ ቆይቷል፡፡ ከተወሰዱ እርምጃዎች መካከል ዘርፉን መለወጥ የተወሰደው እርምጃ ይገኝበታል፡፡ በዚህም መሰረት የመንገድ ሐብት አስተዳደር፣ የመንገድ ሐብት ባለቤትነት፣ ኃላፊነትና የመንገድ ፈንድ በቋሚነት ማሰባሰብ የሚሉ ይገኙበታል፡፡

የመንገድ ፈንድ ጽህፈት በቤት በ1989 ሲቋቋም በዋናነት ለመንገድ ጥገና የሚሆን ፈንድ የማሰባሰብን ዋነኛ ዓላማ አድርጎ ነበር በአዋጅ ቁጥር 66/1989. የተቋቋመው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ፈንድ በማሰባሰብ ለመንገድ ኤጀንሲዎች የማከፋፈልና ፈንዱ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን የማረጋገጥ ሥራ ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

በ2011 በጀት ዓመትም ብር 2,628,710,602.08 ለማሰባሰን አቅዶ በነዳጅ ላይ ከተጣለ ታሪፍ ብር 2,708,895,401.40 ፣ ከተሽከርካሪ ዘይትና ቅባት ብር 3,824,138.13፣ ከመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ ብር 9,800,756.89 ፣ከግምጃ ቤት ሠነድ ግዢ ወለድ ብር 16,500,000 እና በክብደት ላይ የተመሰረተ ዓመታዊ የተሸከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ብር 183,763,047.78 በአጠቃለይ በአመቱ ብር 2,922,783,344.20 **በማሰባሰብ የዕቅዱ** 111.19% ማስመዝገብ ችሏል፡፡

| የገቢ ርዕስ | የ12 ወራት ዕቅድ | የ12 ወራት ክንውን | ንፅፅር በ% |
|---|---|---|---|
| በነዳጅ ላይ ከተጣለ ታሪፍ | 2,400,000,000 | 2,708,895,401.40 | 112.87 |
| ከተሸከርካሪ ዘይትና ቅባት | 3,340,000 | 3,824,138.13 | 114.5 |
| ከመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ | 5,000,000 | 9,800,756.89 | 196.02 |
| ከግምጃ ቤት ሠነድ ግዢ ወለድ | 9,600,000 | 16,500,000 | 171.88 |
| በክብደት ላይ የተመሰረተ ዓመታዊ የተሸከርካሪ ፈቃድ | 210,710,475 | 183,763,047.78 | 82.07 |

**የመንገድፈንድፅ/ቤት**
**ፕሬስመግለጫመስጫቅጽ**
**የኮርፖሬትኮሙዩኒኬሽንዳይሬክቶሬት**

| ማደሻ | | | |
|---|---|---|---|
| ድምር | **2,628,710,602.08** | **2,922,783,344.20** | 111.19 |

በተመሳሳይ ለመንገድ ጥገና እና ደህንነት እርምጃዎች በበጀት ዓመቱ ብር 2,370,978,877.60 ክፍያ ለመፈፀም ዕቅድ ተይዞ ብር 1,756,085,524 ወይም የዕቅዱ 74.07 በመቶ ክፍያ ተፈፅሟል፡፡ ክፊያው የሚፈጸመው ጥገና መካሄዱ በቴኪኒካዊ ኦዲት ስረጋገጥ፣ አማካሪያዎች ሲያረጋግጡና የክፊያ ሰርቲኬት ቀርቦ ትክክለኛነቱ ሲረጋገጥ በመሆኑ የክፊያ ሰርቲፊኬቶች በተቀመጠው መሰረት እየተረጋገጡ አለመቅረባቸው በክፊያ አፈጻጸም ላይ ተጽዕኖ መፍጠሩ ተገምግሟል፡፡

| የበጀት ድልድል | የ12 ወራት በጀት | በ12 ወራት የተፈፀመ ክፍያ | ንፅፅር በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| የመንገድ ጥገና ድምር | 2,370,978,877.60 | 1,757,842,396.49 | 74.07 |
| ለኢመባ | 1,502,959,965.60 | 977,644,824.11 | 65.05 |
| ለክልል | 584,893,130.00 | 571,837,916.31 | 97.77 |
| ለከተማ | 283,125,782.00 | 208,359,656.07 | 73.59 |
| ለመንገድ ደህንነት | 23,337,600 | 0 | 0.00 |
| ለፈንዱ ድጋፍ አገልግሎት | 36,270,000 | 33,261,007.93 | 91.7 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ድምር | 2,430,586,477.60 | 1,791,103,404.42 | 73.69 |

ጽህፈት ቤቱ በሚያደርገው የበጀት ድጋፍ የተከናወኑ ጥገናዎችን በሚመለከት በበጀት ዓመቱ 21,002.26 **ኪ.ሜ መደበኛ ጥገና እንዲሁም** 6,038.62 **ኪ.ሜ ወቅታዊ ጥገና በድምሩ 27,040.88 ኪ.ሜ መንገድ ጥገና ለማድረግ አቅዶ የነበረ ሲሆን** 16,150.00 **ኪ.ሜ መደበኛ ጥገና እንዲሁም** 5,475.60 **ኪ.ሜ ወቅታዊ ጥገና በድምሩ 21,625.60 ኪ.ሜ መንገድ ጥገና በማድረግ በንጽጽር 79.97% ማስመዝገብ ችሏል፡፡**

| **አጀንሲ** | **መደበኛ ጥገና (በኪ.ሜ)** | | | **ወቅታዊ ጥገና (በኪ.ሜ)** | | | **ድምር** | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | **ዕቅድ** | **ክንውን** | **%** | **ዕቅድ** | **ክንውን** | **%** | **ዕቅድ** | **ክንውን** | **%** |
| ኢ.መባ | **11,364.00** | **6,503.00** | **57.22** | **704** | **652** | **92.61** | **12,068.00** | **7,155.00** | **59.29** |
| ክልል | **9,496.41** | **9,507.42** | **100.12** | **5,329.30** | **4,820.08** | **90.44** | **14,825.71** | **14,327.50** | **96.64** |
| **ከተማ** | **141.85** | **139.58** | **98.40** | **5.32** | **3.52** | **66.17** | **147.17** | **143.10** | **97.23** |
| **ድምር** | 21,002.26 | 16,150.00 | **76.90** | 6,038.62 | 5,475.60 | **90.68** | **27,040.88** | **21,625.60** | **79.97** |

*ፈንዱ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን የማረጋገጥ ሥራን በሚመለከት በበጀት ዓመቱ የቴክኒካልና ፋይናንሺያል ኦዲት ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ የቴክኒካል ኦዲትን በሚመለከት፣*

- ለ2011 በጀት ዓመት ከ71 መንገድ ኤጀንሲዎች የቀረቡ ዕቅዶችን በቼክ ሊስቱ መሰረት በመገምገም ትክክለኛ ዕቅድ መሆኑን ማረጋገጥ እና ክፍተት በተገኘባቸው ላይ ግብረ መልስ ተሰጥቶባቸዋል ፡፡ አፈጻጸሙም 85% ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

**የመንገድፈንድፅ/ቤት**
**ፕሬስመግለጫመስጫቅጽ**
**የኮርፖሬትኮሙዩኒኬሽንዳይሬክቶሬት**

- ከመንገድ ኤጀንሲዎች የቀረቡ የ501ክፍያ ሰርተፊኬት ጥያቄዎችን በዕቅዱና በውሉ መሰረት በትክክል መሰራታቸውን በማረጋገጥ በወቅቱ ክፍያ እንዲፈፀም ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም 100% ሆኖ ተመዝግቧል፡፡
- የጥገና አፈፃፀም ሪፖርቶችን በመገምገም ግብረ መልስ ተሰጥቷል፡፡ አፈጻጸሙም 173% ሆኖ ተመዝግቧል፡፡
- ለ4 መንገድ ጥገና ክትትልና ቁጥጥር ስራ አማካሪዎች እንዲቀጠሩ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም 80% ሆኖ ተመዝግቧል፡፡
- የ6 ኤጀንሲዎች የአማካሪ ቅጥር ለማከናወን የመንገድ ኤጀንሲዎች የሚያዘጋጁዋቸውን የጨረታ ሰነዶች ተገምግሟል፡፡ አፈጻጸሙም 100% ሆኖ ተመዝግቧል፡፡
- አማካሪዎች በውላቸው መሰረት ስራቸውን ማከናወናቸውን ክትትልና ቁጥጥር ተደርጓል፤ የአሰራር ክፍተት በተገኘባቸው በ3 አማካሪ ድርጅቶች ላይ እርምጃ ተወስዷል፡፡
- በደቡብ መንገዶች ባለሥልጣን - ዲላ፣ ሶዶና ሆሳዕና ዲስትሪክቶች፣ በሀዋሳ ማዘጋጃ ቤት እና በኢመባ - ዓለምገና ዲስትሪክት በእምድብር ሴክሺን፣ በአማራ ገጠር መንገድ፣ በክልሉ ተጠቃሚ በሆኑ ከተሞች፣ በኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣንና በክልሉ የፈንድ ተጠቃሚዎች ከተሞች የመስክ ምልከታና ግምገማ ተደርጎ በአሰራር ላይ በታዩ ክፍተቶች፡- በጥገና መካተት የሌለባቸው መንገዶች በዕቅድ መካተት፣ የጥገና ጥራት፣ አማካሪዎች በውላቸው መሠረት በቦታው ተገኝተው አገልግሎት አለመስጠት፣ በኮንትራት ውስጥ የሌሉ ስራዎች እየተሰሩ መሆን የአሰራር ክፍተቶች የተስተዋሉ ሲሆን ኤጀንሲው በተገኙት ግኝቶች ላይ ማስተካከያ እንዲያደርግ ግብረ መልስ ተሰጥቷል፣ ክትትልም እየተደረገበት ነው፡፡
- የዘጠኝ ክልል መንገድ ኤጀንሲዎችንና የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤትንየአቅም ግንባታ-ሎጂስቲክና በመሳሪያ(ማሺን) ለመደገፍ ችግራቸውን በመለየት ድጋፍ ለማድረግ መረጃ ተጠናቅሯል፣ የተጠናቀረው መረጃ ለቦርድ ውሳኔ ቀርቧል፡፡
- የፈንዱን በጀት በተሻለ መልኩ ለመንገድ ኤጀንሲዎች በግልፀኝነት ድልድል ለማድረግ፣ የፈንዱ በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ እና የመንገድ ጥገናው ሥራ በተሻለ እንዲመራ ለማድረግ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋርበትብብር የመንገድ መረጃ መሰብሰብ (Road

inventory)፣የመንገድ ሁኔታ ጥናት (Road Condition Survey)፣የመንገድ ጥናት አማራጮች (Road Maintenance Modality)፣የበጀት ቀመር አሰራር(Fund Allocation Formulation)፣ከ10% - 20% ናሙናን መሠረት ያደረገ የቴክኒክ እና ፋይናንሺያል ኦዲት (Technical and Financial Audit) ዙሪያ ጥናት እንዲያደርጉ ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ፣ ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኒዮሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣ ከአዳማ እና ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ጋር የመግባቢያ ሰነድ እና የኮንትራት ስምምነት በመፈራረም ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን የጂማ ዩኒቨርሲቲያቀረበው የቴክኒካልና የፋይናንሺያል ፕሮፖዛል ተገምግሞ ግብረ መልስ ተሰጥቷል፡፡

ፋይናንሺያል ኦዲት፣

- የ2010 በጀት ዓመት 4ኛ ሩብ ዓመት፤ የ2011 በጀት ዓመት 1ኛ ፤2ኛእና 3ኛ ሩብ ዓመት መደበኛ ሂሣብ ኦዲት ምርመራ ተከናውኖ ሪፖርቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር ተልኳል፤ አፈጻጸሙም 100% ሆኖ ተመዝግቧል፡፡
- የ2010 በጀት ዓመት የፈሰስ ሂሣብ ለገንዘብ ሚ/ር ሪፖርቱ ተላልፏል፡፡ አፈጻጸሙም 100% ሆኖ ተመዝግቧል፡፡
- ከኢትዩድያ ነዳጅ ድርጅት እና ከነዳጅ ኩባንያዎች መሰብሰብ ያለበት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡ በሚቀርበው ወርሀዊ ሪፖርት መሰረት ክትትል ተደርጓል፡፡
- በ13 ነዳጅ ኩባንያዎች የሚሰበሰበው ገቢ በየወሩ በሚቀርበው ሂሳብ ሪፖርት መሰረት ተገምግሟል፡፡
- ከመንገድ ጠቀሜታ ከሚሰበሰብ ገቢ ከጅቡቲና ከሱዳን ከሚገቡ ከባድ ተሸከርካሪዎች ኩፖን ሽያጭ ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡ በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት መሰረት ክትትል የተደረገ ሲሆን ከጅቡቲ ከሚገቡ ተሸከርካሪዎች ገቢ ይሰበስብ የነበረው የኢትዮጵያ ባህር ትራንዚት ሎጂስቲክ አገልግሎት ስራውን መስራት አለመቻሉን በመግለፁ እና ገቢንም በወቅቱ ማስገባት ላይ ክፍተት ስለነበረበት ከየካቲት 2011 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ገቢ ተሰብስቦ ለጽ/ቤቱ በወቅቱ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

**የመንገድፈንድፅ/ቤት**
**ፕሬስመግለጫመስጫቅጽ**
**የኮርፖሬትኮሙዩኒኬሽንዳይሬክቶሬት**

- በኢትዩድያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት በኩል የሚሰበሰበውን ዓመታዊ የተሽከርካሪ ክፍያ ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን እንዲያጣራ የተወከለው የሂሳብ አጣሪ ድርጅት ለጽ/ቤቱ ያቀረበው ሪፖርት ተገምግሞ ግብረ መልስ ተሰጥቷል፡፡
- የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ70 መንገድ ኤጀንሲዎች የመጨረሻ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች ላይ ማስተካከያ እርምጃ ተወስዶ ክትትል እየተደረገበት ይገኛል፤
- የመንገድ ፈንድ የውስጥ ኦዲተሮች በዕቅዱ መሠረት በሁለት ቡድን በመሆን በአዲስ አበባ መ/ባ፣ በኦሮሚያ መ/ባ፣ በአማራ ገ/መ/ባ፣ በባህርዳር ከተማ መ/ባ፣በአምቦ፣ በከሚሴ፣ በደ/ማርቆስ፣ በኢንጅባራ፣ በፍኖተ ሠላም፣ በቢሸፍቱ፣ በወሊሶ እና በአሰላከተማ ማዘጋጃ ቤትበመገኘት የ2010 በጀት ዓመት የፋይናንስ አጠቃቀማቸውን ኦዲት ተደርጓል፣
- በውጭ ኦዲት እንዲመረመር የፈንዱን ሂሳብ ጨምሮ የ30 ኤጀንሲዎች ታቅዶ የ34 ተመርምሯል፣ (113%)፡፡
- ከ23 መንገድኤጀንሲየውስጥኦዲተሮችየቀረበ የ2010 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት ተገምግሞ ግብረ መልስ ተሰጥቷል፡፡ የመንገድ ኤጀንሲዎች የውስጥ ኦዲት የ2011 በጀት ዓመት የድርጊት መርሃ ግብር እንዲያቀርቡ በተላለፈው የስምምነት ሰነድ መሰረት ከ20 መንገድ ኤጀንሲዎች ለጽ/ቤቱ የቀረበ ሲሆን ሌሎቹም እንዲያቀርቡ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡(133%)
- መንገድ ፈንድ ከመንገድኤጀንሲዎችጋርባደረገውየውልስምምነት መሠረት የኦዲት ክትትል ለማድረግ በጀታቸውለታለመለትየፕገናዕቅድመዋሉን መከታታል የሚያስችሉ ሠነዶች መካተቱን ገምግሟል፤
- ከተፈቀደ ክብደት በላይ ከሚጣል ቅጣት ገቢ ረቂቅ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲፀድቅ ለትራንስፖርት ሚ/ር በደብዳቤ በመጠየቅ ክትትል ተደርጓል፡፡
- በመንገድ ፈንድ ፋይናንስ መመሪያ መሠረት ለክልል መንገድ ኤጀንሲዎች የተላለፈ የመሳሪያ መተኪያ በጀት ለሚፈለገው ዓላማ መዋሉን ተገቢው ክትትል የተደረገ ሲሆን በመሳሪያ መተኪያ በጀት የተገዙ ማሽነሪዎች መረጃ ዝርዝር ተጠቃሏል፡፡

**የመንገድፈንድፅ/ቤት**
**ፐሬስመግለጫመስጫቅጽ**
**የኮርፖሬትኮሙዩኒኬሽንዳይሬክቶሬት**

- ከሁሉም መንገድ ኤጀንሲዎች ለተውጣጡ98 የሂሳብ ባለሙያዎችና ኦዲተሮች ስለ ፈንዱ ሂሳብ አሰራር እና የሚታዩ የአሰራር ክፍተቶችን ለመድፈን የሚያስችል በቢሾፍቱ ከተማ በመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ባለሙያዎች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡